# የከብቶች ድንች (Fodder Beet)

## መግቢያ

የከብቶች ድንች ወቅታዊ የሆነ የእንስሳት መኖ ሲሆን ዋናው የምግብ ይዘቱ  ሥሩ ላይ ሆኖ ቅጠሉም ለከብቶች ምግብነት ይውላል፡፡ ይህ መኖ ከባህር ወለል ከፍታ 1800-3000 ሜትር ባሉ ቀዝቃዛ አካባቢዎች ይበቅላል፡፡ አሲዳማ (ቀይ አፈር) ለእጽዋቱ መብቀል ተስማሚ ሲሆን ኮትቻና ውሃ የሚተኛበት መሬት እጽዋቱን ዉጤታማ አያደርገዉም፡፡



## የዘር እና የማዳበሪያ መጠን

ለአንድ ሄክታር የመሬት ስፋት ከ5-10 ኪ.ግ ዘር ያስፈልጋል ። በመስመር ሲዘራ በመስመር በመካከል 50 ሳ.ሜ ክፍተት እንዲሁም በተክል መካከል 30 ሳ.ሜ ክፍተት ሊኖር ይገባል፡፡ የማዳበሪያ መጠንም 100 ኪ.ግ ዳፕ/NPS ወይም 100-150 ኩ/ሄክ ፍግ መጠቀም እንችላለን፡፡ የዚህ መኖ ዋናው ምርት ያለው ሥሩ ላይ ስለሆነ በተደጋጋሚ አፈር ማሳቀፍና መኮትኮት ያስፈልጋል።

## የአመጋገብ ሁኔታ

ሥሩ ከተተከለ ከ6 – 7 ወር ውስጥ ተቆፍሮ እና ተከትክቶ (ተቆራረጦ) ከሌላ መኖ ጋር ተደባልቆ ሊሰጥ ይችላል፡፡ሲቆፈር ሥሩ እንዳይጎዳ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ይህ ድንች በኃይል ሰጭ ንጥረ ነገር የበለጸገ መኖ በመሆኑ ለከብቶች በምንመግብበት ወቅት ለመጀመሪያዎቹ ቀናቶችን መጠኑን አነስተኛ አድርገን መመገብ ያለብን ሲሆን ከብቶች አየለመዱት ሲሄድ የመኖው መጠን እየጨመረ ሊሄድ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መኖው ለከብቱ መሰጠት ያለበት ከብቱ ሌላ መኖ ከበላ በኋላ ከሰዓት በኋላ ቢሆን ይመረጣል፡፡

## የዘር ብዜት

የከብቶች ድንች ዘር ለማባዛት ዘሩ ካፈራ በኃላ ሳይነካ ለቀጣይ የምርት ወቅት መቆየት አለበት፡፡ ዘሩ አፍርቶ ቅጠሉን ካራገፈ በኃላ እርጥበት በሚያገኝበት ጊዜ አበባ ያወጣና ፍሬ ያፈራል፡፡ ለዘር ብዜት ቀዝቃዛ ቦታዎች(2700ሜ) ተመራጭ ናቸዉ፡፡ በሄክታር ከ4-5 ኩንታል ዘር መሰብሰብ ይቻላል፡፡

## ምርታማነቱ

የከብቶች ድንች በሄክታር 520-680 ኩንታል እርጥብ ወይም 130 – 170 ኩንታል ደረቅ ምርት መሰብሰብ  ይቻላል ፡፡





## ጥንቃቄ

- ከመጠን በላይ ከተበላ አሲድነት/መርዛማነት አለው
- ጃርት በጣም ያጠቃዋል ስለዚህ መታጠር አለበት
- በተጎዳ መሬት/ለምነቱ አነስተኛ በሆነ መሬት ምርቱ አነስተኛ ነው
- ውሃ በሚተኛበትና ጠንካራ በሆነ መሬት እድገቱና ምርቱ ይገታል
- ውርጭን የመቋቋም ሀይሉ አነስተኛ ነው ፡፡

## ምስጋና

አፍሪካ ራይዚንግ (Africa RISING) ፕሮግራሙ በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ድርጅት (USAID) ገንዘብ የሚደገፍና በተለያዩ አገር አቀፍ እና አለም አቀፍ የምርምር እና የልማት አጋሮች በጋራ የሚተገበር ነዉ፡፡ ለፕሮግራሙ መሳካት አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ በሙሉ የላቀ ምስጋና እናቀርባለን፡፡

## ለተጨማሪ መረጃ

ከንዱ መኮንን
መልካሙ በዛብህ
አበራ አዲ
ስምረት ያሳቡ
ስልክ ፡+251 116172000/2234

This document is licensed for use under the Creative Commons Attribution 4.0 International Licence.    January 2019